# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም:-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሚያዚያ 14 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**መለስ ዜናዊ በምክር ቤት ሲያስፈራራና ዛቻ ሲሰነዝር ዋለ፤**

**ህዝቡ በወያኔ ባለስልጣናት ላይ እርምጃ መውሰድ ጀመረ፤**

**አንድ የወያኔ ባለስልጣን ከግድያ ቢያመልጥም ፎቅ ዘልሎ ለማምለጥ በመሞከሩ አደጋ ደርሶበት ሆስፒታል ገባ፤**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተብዬ ባቀረበው ማብራሪያ መምህራኖችን .....የእስልምና እምነት ተከታዮችን...... የማህበረ ቅዱሳን አባላትን እና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ሲያንጉዋጥጥ እና ሲያጥላላ ብሎም ሲያስፈራራ መዋሉ ተደመጠ::

ማክሰኞ ሚያዝያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም ከምክር ቤቱ አባሎች ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተገኘ የተባለው ይሄው ግለሰብ በቅርቡ ለመምህራን ተደረገ የተባለውንና ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት በካድሬዎች ቅስቀሳ ሲደረግበት የነበረውን የደመወዝ ጭማሪ ከመምህራኑ ብርቱ ተቃውሞ ስለገጠመውና አመጽም ሊያስነሳ ይችላል ብሎ በመፍራቱ ሽምጥጥ አድርጎ ክዶ ጭማሪ ሳይሆን የደረጃ እድገት ማስተካከያ ነው በማለት መልስ በመስጠቱ ከፍተኛ ትዝብት ላይ መውደቁ ታውቆዋል::

ለወያኔ ተላላኪ በሆነው የመምህራኑ ማህበር በኩል ሳይቀር የደመወዝ ጥያቄ ከሁለት እና ከዚያም ዓመት በላይ ለሆነ ግዜ ሲያቀርቡ የነበረውን የመምህራኑ ወሳኝ ብሶት ወደጎን በማለት ጥያቄ አቅርበው አያውቁም በማለት እያጣጣለ በመናገሩ መምህራኑ ክፉኛ እንዳዘኑና ወደ ሌላ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማድረግ እየተገደዱ መሆኑም ታውቆዋል::

በእብሪት እና በማን አለብኝነት እንደፈለገው እና እንዳሻው ኢትዮጵያዊነት ባህል በጎደለው ገለጻ መምህራኑን ሲያንጉዋጥጥ እና ሲዘልፍ የዋለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በቅርቡ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም በድሬዳዋ ስብሰባ ተደርጎ መምህራኑ አስቸኩዋይ የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግለት ይሕ ባይሆን

EthioLion.Com

አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስዱ ባስጠነቀቁ ጥቂት ግዜ የደመወዝ ጭማሪ ተደረገ ብሎ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ጥረት ያደረገ ቢሆንም በመምህራኑ እና በህዝብ ዘንድ ውድቅ በመደረጉ የተደናገጠው መለስ ዜናዊ መልሶ የእርከን መስተካከያ እንጂ ጭማሪ አይደለም ብሎ መዘላበዱ እጅግ የሚያሳፈር እና የሚያሳዝን መሆኑን መምህራን በብስጭት እየገለፁ ይገኛሉ::

ዛሬ አንድ ኩንታል ጤፍ ከ1800 ብር በላይ ባናጠረበት...... የአንድ ሊትር ዘይት ዋጋ ከ50 ብር በላይ በዘለለበት....... በአሁኑ ወቅት ኑሮን መቋዋቋዋም አቅቶናል የደመወዝ ጭማሪ ይደረግልን ብለው መምህራኑ ያቀረቡትን ውድቅ አድርጎ የእርከን ጥያቄ ነው በማለት ለማድበስበስ ቢሞክርም አሁንም ጥያቄው ተዳፍኖ የእሳት ረመጥ ሆኖ እንዳለ መምህሩ እየተናገረ ይገኛል:: ተደረገ የተባለው የደመወዝ ጭማሪ መምህሩን ለሌላ ወጪ እና እንግልት የሚዳረገው እንጂ ጥቅም እንደሌለው በመግለፅ አብዛኛው መመህር የስራ ማቆም አድማ በማድረግ ተቃውሞ ለሳምንታት ያደረገ መሆኑ እየታወቀ የመላ መምህራኑን ጥያቄ የጥቂት ያውም የ500 ብቻ አድርጎ ማቅረቡ አሳዛኝ እና የወረደ ገለጻ ሲሉ መምህራኑ በንዴት ሲገልጹ ተደምጠዋል::

የደመወዝ ጭማሪ ተደረገ ተብሎ ለአንድ ሳምንት ያህል ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ እናገኝበታለን ብለው ሲባዝኑ የነበሩት የወያኔ ቡድን ካድሬዎች ከመምህራኑ ባጋጠማቸው ብርቱ ተቃውሞ የተነሳ ጭማሪው ማስተካከያ ነው ብለው መግለጫ እንዲሰጡ በተደረገ ጥቂት ቀናት ውስጥ መለስ በምክር ቤት ተገኝቶ ማብራሪያ መስጠቱ ወያኔ አሁንም ውስጡ በፍርሀት እየታመሰ መሆኑን የሚያመላክት ነው ተብሎዋል::

በሀገሪቱ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ ግማሽ ሚሊዮን የሚቆጠሩ መምህራን ባሉበት ሀገር 500 ብቻ ተቃውሞ አሰሙ ብሎ በይፋ በአደባባይ መገልጹ ህዝብንና መምህራኑን ጭምር የናቀ በመሆኑ መምህራኑ ያነሳው የመብት ጥያቄ ዳር እስኪደርስ ድረስ በተቃውሞውና በስራ ማቆሙ አድማ እንደሚገፋበት እየገለጹ ይገኛሉ::

የመብት ጥያቄ ያነሱትን መምህራኖች የነውጥ ናፋቂ አስመስሎ ያቀረበው መለስ ዜናዊ አሸባሪ ብሎ ከፈረጃቸው የተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖች ጋር እየለጠፈ ሲያስፈራራና ሲዝትባቸው ከመዋሉም በላይ ምድረ ነውጠኛ በየትምህርት ቤቱ አመጽ ለማስነሳት ሰጥሩ ነበር ሲልም ሲወነጅላቸው ተደምጦዋል::

ከችሎታ ይልቅ የወያኔ አባል መሆን ቅድሚያ የሰጠው ዘረኛው ቡድን .....የትምህርት ጥራት ከቀን ወደ ቀን .......ከግዜ ወደ ግዜ እያሽቆለቆለ መሆኑን ነባር እና አስተዋይ መምህራኖች ምክር ሲለግሱ አልሰማም ሲል የከረመው ወያኔ አንድ ትውልድ ገደል ከከተተ በሁዋላ ዛሬ መምህራኑ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ ጥያቄያቸውን ውድቅ ለማድረግ ብሎም ጨርሶ ለማጥፋት ሲል ችሎታ የሌላቸው እያለ መዘለፉ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉም እየገለጹ ናቸው::

በሀገሪቱ የትምህርት ጥራት እየወረደና እየወደቀ ነው ብለው ምክር ሲለግሱት የነበሩትን መምህራኖች የልማት እንቅፋቶች ......የወደቀው ስርዓት ናፋቂዎች......እያለ ሲያብጠለጥላቸው እና ሲያወግዛቸው እንዳልነበር የስርዓቱ ዋነኛ ምሰሶ ናቸው የተባሉ የወያኔ አባሎች ችሎታ ሳይሆን

የፖለቲካ ተሳትፎ ብቻ ስላላቸው ሲክባቸውና ሲያወድሳቸው እንዳልነበር ዛሬ መልሶ ለትምህርት ጥራት ተቆርቁዋሪ መስሎ መታየቱ የሚያሳዝን ነው ሲሉም እነዚሁ ወገኖች ይገልጻሉ::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በዕለቱ ባደረገው ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ ከተካተቱት ውስጥ አንዱ የእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ የሰነዘረው ዛቻ ሲሆን በማያገባውና በማያውቀው ሁኔታ እምነቱን እየከፋፈለና እየነጣጠለ ሲተች እንደነበርም ተደምጦዋል::

በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በእስልምና እምነት ተከታዮች እና አባቶች ዘንድ የተነሳውን ጥያቄ ለማድበስበስ እና አስፈራርቶ ለማዳፈን ሙከራ እያደረገ ባለበት በዚህ ወቅት ለመጀመሪያ ግዜ የአልቃይዳ ህዋስ በሀገሪቱ ተገኝቶዋል ብሎ መግለጫ መስጠቱ ሰውዬው ግዜያዊ እና ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘ ት ሲል ብቻ በሀገሪቱ የሌለና ያልተፈጠረውን በሀሰት እየነዛ የህዝቡን ሰላም ለመንሳት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው ሲሉም ምሁራኖች ትችት እየሰነዘሩበት ይገኛል::

በርከታ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ አማኝ የሆኑበትን የእስልምና እምነት ተከታዮች ለመምታት ብሎም አንገት ለማስደፋት የተለያዩ ስልቶችን ሲጠቀም የቆየው መለስ ዜናዊ ሰሞኑንም የሚፈልጋቸውን ሰዎች አፍሶ ለማሰር እንዲያመቸው የአልቃይዳ ህዋስ በአርሲና በባሌ ተገኝቶዋል በማለት መግለጫ መስጠቱ ሆን ብሎ የፈጠረው ዘዴ መሆኑን የተናገሩት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች መለስና ቡድኑ በአሁኑ ወቅት የፍርሀቱ ምንጭ ምን እንደሆነ ባይታወቅም ከፍተኛ ችግር ያለበት እንደሆነ የሚያሳይ ነው ሲሉም ሲናገሩ ተደምጠዋል::

ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ወያኔ በባሌና በአርሲ አከባቢ የአልቃይዳ አባሎች ናቸው ያላቸውን 12 ሰዎችን ማሰሩን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ለማወቅ ተችሏል:: ከዚህ ቀደም በበደኖ ከ50 ሰው በላይ ዘግናኝ በሆነ መልኩ ጨፍጭፎዋቸ ለውሀ በተቆፈረ ጥልቅ ጉድጉዋድ ውስጥ ቀብሮዋቸው መልሶ ድርጊቱን የፈፀመው ሌላ ወገን እንደሆነ አስመስሎ በማቅረብ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባዝን የከረመ መሆኑን ያስታወሱት እነዚሁ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች አሁንም የወያኔ ስርዓት በውስጥ እና በውጭ አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ ለግዜያዊ ፋታ ማግኛ ይሆነኛል በሚል የአልቃይዳ ህዋስ ተገኝቶዋል በማለት ዜጎችን እያፈሰ ለእስር እየዳረጋቸው መሆኑ ታውቆዋል::

በሙስና የነቀዙ ባለስልጣናትን ሰብስቦና አቅፎ መልካም አስተዳደርን አመጣለሁ እያለ እምቡዋ ከረዩ የሚለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የውጭ መንግስታትን ለመሸወድ እና ለማታለል ብሎም የህዝቡን ድጋፍ ለማግኘት ሲል ኪራይ ሰብሳቢነትን አጥፍቼ ልማታዊነትን አሰፍናለሁ እያለ የምላስ አክሮባት ቢሰራም እየሆነና እየተነገረ ያለው ፍጹም የማይገናኝ መሆኑን የለጋሽ ድርጅቶች እና የዓለም አቀፍ ተቋዋሞች እየገለጹ ይገኛሉ::

በቅርቡ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋዋም የሆነው ድርጅት እንደገለጸው ከሆነ በአምስት ዓመቱ ትራንስፎርሜሽን እና እቅድ ውስጥ የተያዙት ፕሮግራሞች ህዝቡን ለማደናገሪያ እንጂ ሊፈፀሙ እንደማይችሉ በመግለጽ እቅዱን እንደገና እንዲያየውና እንዲከልሰው መግለጻቸው ይታወሳል::

በዚሁ በምክር ቤት በተደረገው ጥያቄና መልስ ላይ ብቸኛው የመድረክ ተወካይ የሆነው ግርማ ሰይፉ ለሚያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች አግባብ ያለው መልስ ከመስጠት ይልቅ አፉ እየደረቀ....ምላሱ

EthioLion.Com

እየተጣበቀ......ደጋግሞ በውሀ እያራሰ የውሸት ፕሮፖጋንዳውን ሊግት ቢሞክርም የራሴ ናቸው የሚላቸው የምክር ቤት አባሎች ጭምር ከፍተኛ ቅሬታ ተሰምቶዋቸው እንደዋለ ከምክር ቤት ሲወጡ ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በሌላ ዜና የወያኔ ቡድን በውስጥ የእርስ በርስ ሽኩቻ እየዳከረ ባለበት በዚህ ግዜ ህዝቡ በሚጠላቸው ካድሬዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በይፋ መንቀሳቀስ መጀመሩ ተጠቆመ::

ሰሞኑን በአዲስ አበባ የአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 ስራ አስፈፃሚ(ሊቀመንበር) በሆነው ግለሰብ ላይ ብሶት የወለደው ወጣት ሚያዚያ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት ላይ ከጥበቃ በቀማው መሳሪያ ሊገድለው ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት እንደቀረ ታወቀ::

በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ወንጀል ሲፈጽም የኖረው ይሄው የወያኔ ካባር ባለስልጣን በታክሲ ተራ አስከባሪነት እየሰራ በነበረው ወጣት ላይ እንግልት እና ስቃይ በማደረሱ የተበሳጨው ወጣት በንዴት ሊገድለው ሙከራ አድርጎ መሳሪያው ነክሶ ሊተርፍ እንደቻለ ታውቆዋል::

ከግድያ ለጥቂት ያመለጠው ሻረው ዘለቀ የተባለው ነባር ባለስልጣን መሳሪያ ይዞ የመጣው ወጣት ሊገድለው ቃታ በሳበት ወቅት በድንጋጤ ከሁለተኛ ፎቅ ላይ ዘልሎ ለማምለጥ ቢሞክርም በእግሩ ላይ የመሰበር አደጋ እንደደረሰበትና በግዜው ህይወቱን ስቶ ተበለሻሽቶ ወደ ህክምና ማዕከል እንደተወሰደም ለማወቅ ተችሎዋል::

ወጣቱ በተደጋጋሚ ግዜ ከሁለት ዓመት በላይ ያቀረበው አቤቱታ እንዲፈጸምለት ቢወተውትም ምላሽ ካለማግኘቱም በተጨማሪ በዚኔ እየተባለ በጥበቃ ሲያባርረው የነበረ መሆኑን የጠቆሙት ጉዳዩን የሚያውቁት ወገኖች በዛም ዕለት ለመጨረሻ ግዜ ሊያስጨርሰው በሜድ ላይ እንዳለ ትዕግስቱ ስላለቀበት ከጥበቃው ላይ በመቀማት ራሽያ ሰራሽ በሆነው ክላሽን መሳሪያ ሊገድለው ሙከራ ቢያደርግም መሳሪያው ነክሶበት ሳይሳካለት እንደቀረና ለእስር እንደተዳረገ የደረሰን የአይን እማኞች ጥቆማ ገልጾዋል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በወያኔና በ አጫፋሪዎቹ የአማራና የደቡብ ክልል እየተባሉ በሚጠሩት አከባቢዎች የወያኔ ባለስልጣናት በዜጎች ላይ በሚያደርሱት አስተዳደራዊ በደል እና በሚፈጽሙት ግፍ የተበሳጩ ሰዎች ካድሬዎችን ከመደብደብ እስከ መግደል መድረሳቸው እየተነገረ ይገኛል::

በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ዜጎች በወያኔ ካድሬዎች ላይ ባላቸው ከፍተኛ ጥላቻ የተነሳ መግባባት አቅቶዋቸው ገሚሱ በዱላ ሰደበድብ ገሚሱ በመሳሪያ እየገደለ እንደሚገኝ የገለፀው የደረሰን ዘገባ የቅዳሜ ሹር እለት ሚያዚያ 6 ቀን 2004 ዓ.ም በፍቼ ከተማ ገበያ መሀከል የአንድ ቀበሌ ሊቀመንበርን ወጣቱ ተባብሮ በዱላ ቀጥቅጦ ከፍተኛ ጉዳት እንዳደረሰበት ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

በአካባቢው ወጣቶች እና ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈጽም የነበረው ይሄው ግለሰብ በዕለቱም ነጋዴዎችን በመሳሪያ እያስፈራራ ሲሳደብ ያደመጡ ወጣቶች ተበሳጭተው በዱላ ከጭንቅላት እስከ ቁርጭምጭሚት.....ከጀርባ አጥንት እስከ ቅልጥም ድረስ እየመላለሱ በመደብደባቸው ከፍተኛ አደጋ





EthioLion.com

**አድርሰውበት ጥለውት ቢሄዱም አንጀቱ ያረረው ህዝብም አይቶ እንዳላየ በመሆን ወደ ህክምና ማዕከል የሚወስደው ጠፍቶ መታየቱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።**

EthioLion.Com